**MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION**

**ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት**

P. O. Box 55321, Washington, DC 20040-5321
Tel: (202)-677-0094
Web: http//www.moreshwegenie.org/



## የሕዝብ ያልነበረው «የኢትዮጵያ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት»፣ የትግሬ-ወያኔ ቡድን የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜያዊ አዋጅ ባለማጽደቅ የሕዝብ መሆኑን ማረጋገጫው ዛሬ ነው!

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚባለው የሕዝብ ሆኖ አያውቅም። የሕዝብ ባለመሆኑም፣የሕዝብ መብትና ጥቅምም ሠርቶ አያውቅም። የሕዝብ ጉዳዮችም ሲያስፈጽም ኖሮ አያውቅም። እያስፈጸመ ያለው የትግሬ-ወያኔዎችን አገርና ትውልድ አጥፊ የሆኑ ተግባሮችን ነው። ሲያስፈጽም የኖረውም ኢትዮጵያን ለመበታተንና ዐማራን ለማጥፋት ዓላማ አድርገው የተቀየሱ ፖሊሲዎችና መመሪያዎችን ነው። ባጭሩ ምክር ቤቱ የትግሬ-ወያኔ ጉዳይ አስፈጻሚ በመሆን  ላለፉት 27 ዓመታት የኢትዮጵያን ነባር ታሪክ፣ የሕዝቡን አንድነት፣ በአገሪቱ ረጅም ታሪክ ውስጥ በሕዝቡ የወል ጥረት የተገነቡ ዕሴቶችን ሲንድ መኖሩ ግልጽ ነው።

የትግሬ-ወያኔ ዘረኛ ቡድን፣በጦር መሣሪያ ሥልጣን ይዞ፣ በመሣሪያ ኀይል ሥልጣን ላይ የቆየ እና በዚህም ረግጦና አፍኖ ለመቀጠል የወሰነ በመሆኑ፣ ሕዝቡ አገዛዙ መሮትና አንገሽግሾት ላለፉት ሦስት ተከታታይ ዓመታት ባካሄደው ሕዝባዊ አመጽ፣ የአገዛዙ የአፈናና የዕመቃ መዋቅሮች እንደበፊቱ ተግባራቸውን ሊወጡ ከማይችሉበት ደረጃ  ላይ አድርሶታል። የሕዝቡ ቁጣና አመጽ  የአአገዛዙ ዋነኛ የማፈኛ መዋቅር ከሆነው አጋዚ ሠራዊት ጥይት የበለጠ የሰፋና የጠነከ በመሆኑ፣ ሊቋቋመው ባለመቻሉ በግፍ አስሮ ለዓመታት ያሰቃያቸውን ሰዎች ተገዶ እንዲፈታ ሆኗል። ይህም በተከታታይ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ ማዕበል የአገዛዙን የሥልጣን ማስጠበቂያ አውታሮች ከመሠረታቸው እንዲናጉ በማድረጉ እስረኞችን ከመፍታት በተጎዳኝ፣ ዕድሜውን ለማራዘምና የአፈና መዋቅሮቹን በአዳዲስ መንገድ ለማጠናከር እንዲያመቸው ባንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሦስት ጊዜ አስቸኳይ አዋጅ እንዲያውጅ አስገድዶታል። ይህ ሰሞኑን የታወጀው አዋጅ እመራበታለሁ እያለ የሚመጻደቅበትን ሕገመንግሥት በሚጻረር መልኩ እንዲታወጅ የሕዝቡ አመጽ አስገድዶታል። «ከፈረሱ ጋሪ ይቅደም» የሆነበት ወያኔ ይህን አፋኝ አዋጅ፣ የተወካዮች ምክር ቤት ተብየው  እንዲያጸድቅለት ቀጠሮ ይዟል።

ይህ አዋጅ ጸደቀም አልጸደቀም በሕዝቡ እንቅስቃሴ ላይ ሊያመጣ ይችላል የሚለው አዎንታዊ ተጽዕኖ የለም። በሕዝብ ስም  ጸደቀ  መባሉ ግን አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ፣ የምክር ቤቱን አባሎች እንደ ሕገኛና ሙሉ ሰው ሳይሆን፣ እንደቅጥረኛና ጎደሎ አድርጎ የሚያስቆጥር ነው። ይህም ለራሳቸውም ሆነ ለቤተሰቦቻቸው ታሪክ የጎደፈና የቆሸሸ እንዲሆን ያደርገዋል። በሌላ በኩል የአዋጁ መጽደቅ፣ የሕዝቡን ተቃውሞ ከማሳደግ ጎን፣ ዓለምአቀፋዊ ድጋፉ ከፍ እንዲል የሚያደርግ እንደሆነ ከጅምሩ እየተስተዋለ ነው። በመሆኑም አዋጁ ጸድቆ ለውጥ ሊያመጣ ስለማይችል፣ ዓላማውን ለማይመታ ጉዳይ ከሕዝብ

## የሕዝብ ያልነበረው «የኢትዮጵያ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት»፣ የትግሬ-ወያኔ ቡድን ያወጀውን አስቸኳይ ጊዜያዊ አዋጅ ባለማጽደቅ የሕዝብ መሆኑን ማረጋገጫው ዛሬ ነው!

ከምትቃረኑ፣ አዋጁን ባለማጽደቅ ከሕዝብ ጋር በመቆም ታሪካችሁን ባለቀ ሰዓትም ቢሆን እንድትሠሩ ሕዝባችን ይጠይቃችኋል። ትውልዳችሁን ከተከታታይ ውርደትና ሀፍረት አድኑ እያለም ጥያቄው ያቀርብላችኋል። ከሕዝብ ጎን የመቆምና ያለመቆም ምርጫ ቀርቦላችኋል። ምርጫው ግን የእናንተ ነው። ከሕዝብ ጋር ቆሞ አኩሪ ታሪክ ሠርቶ ማለፍ፤ ወይም ከጠፊውና አጥፊው ቡድን ጋር ቆሞ የትውልድ አሳፋሪ ተጠቃሽ መሆን!

ይህን አፋኝ አዋጅ፣የምክር ቤቱ አባላት አጸደቁትም አላጸደቁትም፣የሕዝቡን አመጽ ያቆማል ተብሎ አይታሰብም። ሆኖም የትግሬ-ወያኔን ዘረኛ አገዛዝ ማስቀጥል ግቡ አድርጎ የተነሳውን አዋጅ በማጽደቅ፣ ሕዝብ እንዲገደልና እንዲሰቃይ ለደቂቃም መፍቀድ ማለት የምክር ቤቱ አባሎች የሕዝብ እንዳልነበሩ ሁሉ፣ በዚህ ባለቀም ሰዓት ከሕዝብ ጋር ሊያጋቸው የሚችለውን ዕድል የዘጉት መሆኑን ያረጋግጣል። ይህ አዋጅ እንዲጸድቅ ካደረጉም፣ የሕዝቡ ጠላት ወያኔ  ብቻ ሳይሆን፣ እነርሱ መሆናቸውን  ያላንዳች ብዥታ በራሳቸው ላይ የእምነት ቃል የሰጡ መሆናቸውን ማሳያ ነው። እውነተኛ የሕዝብ ልጆች ነን ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ ይህን አዋጅ ባለማጽደቅ ከሕዝብ ጎን ሊቆሙ ይገባል። ይህን አዋጅ ማጽደቅ ቀርቶ ሊያጸድቁ ያሰቡ ካሉ፣የሕዝብና የአገር ጠላቶች ናቸውና የሕዝባዊ እንቅስቃሴ መሪዎችና ምላተ-ሕዝቡ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ መዘጋጀት ለነገ የሚባል አይሆንም። ካሁን በኋላ የሕዝቡ ጠላት ወያኔ ብቻ ሳይሆን፣ ለወያኔ ዓላማ ማስፈጸሚያ የቤት ሥራ የሚሠሩት ቡድኖችና ግለሰቦች መሆናቸው ታውቆ፣ በእንደዚህ ባሉት ግለሰቦችና ቡድኖች ማኅበረሰቡ ከማኅበራዊ ጉዳዮች ከማግለል ጀምሮ ልዩ ልዩ ቆጥቋጭ እርምጃዎችን በመውሰድ ለትውልዱ የማይረሳ ትምህርት ሊሰጥ ግድ ይለዋል።

ከእርምጃው በፊት ግን፣የእያንዳንዱ ወረዳ ሕዝብ፣ ወረዳውን ወክለው ላሉት ሰዎች ይህን አገርና ሕዝብ አጥፊ የሆነ አዋጅ እንዳያጸድቁ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት። የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሙያ ማኅበራት፣ የወጣትና የሴቶች ማኅበራት፣ የሲቪክ ድርጅቶች፣ ታዋቂና የኪነጥበብ ሰዎች፣ መምሁራን፣ ተማሪዎች፣ ነጋዴዎች፣ ገበሬዎች፣ ደራሲዎች፣ ወዘተ በቡድንና በግል ለተወካዮች ምክር ቤት አባሎች ይህን የአጋዚ ሠራዊት እንዳሻው ፣ከሞሶሎኒ በከፋ ሁኔታ ሕዝብን የሚጨፈጭፍና የሚያሰቃይ ዘረኛ ፋኖ ነፍሰበላ አውሬ ያሻውን እንዲያደርግ የሚፈቅድ አዋጅ እንዳያጸድቅ ከመጮህ ባሻገር፣ ተቃውሞውን እንዲያሰማ ይጠበቃል።

ሕዝባዊ ትግሉ ወያኔን ሳይጥል አይበርድም!

ሠፊው ሕዝብ ያሸንፋል!